

# ራሄል

- ራሄል የአባቷን የላባን በጎች የምትጠብቅ እረኛ ነበረች። እረኞች በጎቻቸውን ውሀ ወደሚያጠጡበት ጉድጓድም በጎቿን ይዛ ትመጣ ነበር። በዚህ ቀን ደግሞ እርሷ በጎቿን ውሃ በምታጠጣበት ጉድጓድ አጠገብ የአክስቷ ልጅ ያዕቆብ ገኝቷል።

- የመጣውም ከወንድሙ ኤሳው ሸሽቶ ሲሆን እናትዬው ዘመዶቿ ወዳሉበት ምድር እንዲሄድ ነግራዋለች። ቀደም ብለው በውሃ ጉድጓዱ በጎቻቸውን ውሃ ሲያጠጡ  የነበሩ እረኞች ከርቀት የምትታየውና ወደውሃ ጉድጓዱ እየመጣች ያለችው የላባ ልጅ ራሄል እንደሆነች ለያዕቆብ ነገሩት።

- በጉደጓዱ አፍ ላይም ትልቅ ድንጋይ ተገጥሞበት ነበር። ያዕቆብ ድንጋዩን ካንከባለለ በኋላ የራሄልን በጎች ውሃ አጠጣቻቸው። ራሄልን ከሳማት በኋላም አለቀሰ። ማን እንደሆነም ነገራት። ከዚያም ለአበቷ ነገረችውና ከቤት ወጥቶ ተቀበለው።

- ለአንድ ወር ያህል ላባን ካገለገለው በኋላ ስለደሞዝ ተወያዩ። ታዲያ በዚህን ጊዜ ያዕቆብ ከላባ ትንሽ ልጅ ከራሄል ጋር ፍቅር ይዞት ነበር።  ራሄል ከታላቅ እህቷ ከሊያ ይልቅ ቆንጆ ነበረች። ያዕቆብም ላባን ልጁን ራሄልን ሚስት እንድትሆነው  የሚሰጠው ከሆነ  ሰባት አመት ሊያገለግለው ተስማማ። ያዕቆብ ራሄልን በጣም ይወዳት ስለነበር ሰባቱ አመት ጥቂት ሆነበት።

- ከሰባቱ አመት ፍፃሜ በኋላም  ያዕቆብ ወደላባ መጥቶ በስምምነታቸው መሠረት ከራሄል ጋራ ያጋባው  ዘንድ ጠየቀው። የሚወዳትን ራሄልን የሚያገባበት ጊዜ ደረሰ። ታዲያ በሠርጉ ቀን እንደ አካባቢው ባህል የሙሽራይቱ ፊት ሙሉ በሙሉ ተሸፍኖ ስለነበር ያዕቆብ የሚያገባው ራሄልን  ይሁን ወይንም ታላቅ እህቷን ሊያን  ለማወቅ የሚችልበት ምንም አይነት መንገድ አልነበረም።

- በነጋታው የሙሽራይቱ ፊት ተገልጦ ሲመለከት እንደተታለለ ተረዳ! ያገባው የሚወዳትን ራሄልን አልነበረም። ሊያን እንጂ! አባትዬው የአገሩን ባህል እንዲህ ሲል ነገረው፣ “ታላቂቱ እያለች ታናሺቱ ማግባት አትችልም። ታላቂቱ ያላገባች ከሆነ ቅድሚያ ለታላቂቱ ይሰጣል።”

- ራሄልን ለማግባት ሰባት ዓመት መጠበቅ ይኖርበት ነበር። ላባ ሌላ ተጨማሪ ሰባት ዓመታት የሚያገለግለው ከሆነ ራሄልንም ጨምሮ እንዲያገባት እንደሚፈቅድለት ለያዕቆብ ገለፀለት። ስለዚህ ከሳምንት በኋላ ሌላ የሰርግ ስነስርዓት ተፈፀመ። ራሄልም የያዕቆብ ሚስቱ ሆነች።

- ያዕቆብ አሁን ሁለት ሚስቶች አሉት። ለሁለቱም ደግሞ የሚያገለግሏቸው ሴት አገልጋዮች ነበሯቸው። ከራሄል በስተቀር ሊያና የያዕቆብ ሚስቶች አገልጋዮች ሁሉም ልጆችን ለያዕቆብ እየወለዱለት ነበር። ራሄል ግን ምንም ልጆች አልነበሯትም። በአጠቃላይ አስር ልጆች ከተወለዱ በኋላ እግዚአብሔር ራሄልን አሰባት። ወንድ ልጅም ወለደች። ስሙንም ዮሴፍ ብላ ጠራችው። ዮሴፍ በአባቱ በጣም የሚወደድ ልጅ እንደደሚሆን የታወቀ ነው። ምክንያቱም እርሱ የተወለደው እጅግ በጣም ከሚወዳት ሚስቱ ከራሄል ነውና።

- ሀያ ዓመታት ካለፉ በኋላ ያዕቆብ ከላባ መለየት ፈለገ። በመካከላቸውም ስምምነት አደረጉ። ይህም ስምምነት ያዕቆብ ዥንጉርጉር የሆኑትንና ምልክት ያለባቸውን በጎች ይወስዳል። ላባን ደግሞ ምንም ምልክት የሌለባቸውን በጎች ይወስዳል። በጎቹ ሲወልዱም ምልክት ያለባቸውና ዥንጉርጉሮቹ በጎች በሙሉ ጤነኞችና ጠንካሮች ነበረ። ታዲያ ያዕቆብ በዚህ መንገድ ብዙ በጎችን ማግኘት ቻለ። ያዕቆብ ለበጎቹ ሲል ለስድስት ተጨማሪ ዓመታት ላባን ካገለገለው በኋላ ላባ ከሚስቶቹ ከሊያና ከራሄል እንዲሁም ከልጆቻቸው ጋር እንዲሄድ ፈቃደኛ አልበረም። ስለዚህ ያዕቆብ በምስጢር ላባን ሳያውቅ መንገድ ጀመረ። መንገድ ከመጀመራቸው በፊት ራሄል በአባቷ ቤት ውስጥ ከነበሩት የአባቷ ጣኦታት ጥቂቶችን ሰረቀች።

- ከሶስት ቀን በኋላ ላባ ያዕቆብ ያለውን በሙሉ ይዞ እንደተጓዘ ሰማ። እነርሱ ላይ ለመድረስም ሰባት ቀን ፈጀበት። ታዲያ ያዕቆብንና ከእርሱ ጋር ያሉትን ለመያዝ እየገሰገሰ ባለበት ወቅት እግዚአብሔር በመንገድ ላይ ተገናኘውና በያዕቆብ ላይ አንዳችም ጉዳት እንዳያደርስበት አስጠነቀቀው። በያዕቆብ ላይ ከደረሰበት በኋላ ያዕቆብን ወቀሰው። ለዚህም ምክንያቱ የላባ ጣኦታት መጥፋታቸው ነበር። ያዕቆብም እንደሚፈልግለት ነገረው። ሆኖም ጣኦታቱን ራሄል በተቀመጠችበት ግመል ኮርቻ ስር ደብቃቸው ስለነበርና ከግመሏ ስላልወረደች ጣኦታቱ ሊገኙ አልቻሉም።

- ላባና ያዕቆብ ከተወያዩ በኋላ ተስማሙ። ከዚያም ላባ ልጆቹንና የልጅ ልጆቹን ስሞ ተሰናበታቸው። ያዕቆብና ቤተሰቡ ግን ወደ ትውልድ መንደሩ ጉዟቸውን ቀጠሉ።

- ወደ ትውልድ መንደሩ አቅራቢያ በተዳረሱ ጊዜም ከዚህ ቀደም ደጋግሞ ካታለለው ከወንድሙ ኤሳው ጋር ተገናኙ። በዚያን ጊዜ ኤሳው ከእርሱ ጋር 400 ሰዎች ነበሩ። አመጣጡ ሊጎዳቸው በማሰብ ነበር። ያዕቆብም ነገሩ ስላላማረው ለወንድሙ ኤሳው ብዙ እንስሶችን በስጦታ መልክ አስቀድሞ ላከለት። ቤተሰቦቹን ከእርሱ በኋላ አደረጋቸው። በመጀመሪያ የሴት አገልጋዮችን ከዚያ በመቀጠልም ሊያና ልጆቿን በመጨረሻም ራሄልንና ልጇን ዮሴፍን ከሁሉ መጨረሻ አደረጋቸው። ራሄልና ዮሴፍ ምንም ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚችለውን ጥንቃቄ ሁሉ አደረገ።

- አሁን በትክክል እየጠበቀው ያለው ነገር ከወንድሙ ከኤሳው ጥቃትን ነበር። ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ሲፀልይና ከእግዚአብሔር ጋር ሲታገል አደረ። እግዚአብሔርም በዚያ ስፍራ ስሙን ቀይሮ እስራኤል ብሎ ጠራው። በተከታዩ ቀን ከወንድሙ ኤሳው ጋር ተገናኙ። እንዳሰበው ሳይሆን ወንድሙ በይቅርታ መንፈስ ተገናኘው። ይዞለት የመጣውን ስጦታም በግድ ተቀበለው።

- ራሄል ሁለተኛ ልጅ ወለደች። ሆኖም ያንን ልጅ በምትወልድበት ወቅት እሷ ሞተች። እየሞተች እያለችም ልጇን “ቤንኦኒ” ብላ ሰየመችው። ትርጉሙም “የሐዘን ልጅ” ማለት ነው። ያዕቆብ ግን “ቢንያም” ብሎ ሰየመው። ትርጉሙም “የቀኝ እጅ ልጅ” ማለት ነው። አሁን ያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች አሉት። ከእነኝህ አስራ ሁለት የያእቆብ ልጆች የተገኙትን ዘሮች አስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ብለን እንጠራቸዋለን።

*ስለራሄል በዘፍጥረት ምዕራፍ 29 እስከ ምዕራፍ 33 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ጨምራችሁ ማንበብ ትችላላችሁ።*